

## 37-1

# እግዚአብሔር ከእኛ ምን ይፈልጋል

***ራስን ዝቅ የማድረግ ሕይወት እንዲኖረን***

“እግዚአብሔር የተናገረው በሙሴ አማካይነት ብቻ ነውን? በእኛስ አማካይነት ተናግሮ የለምን?” (ዘሁልቁ 12፥2)። ይህ ንግግር ሚሪያምና አሮን በሙሴ ላይ ያሰሙት ሃሜት ነው። ይህን የሚመስሉ ብዙ ድምጾች በዘመናችንም ይሰማሉ። አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል፥ “የፈውስ ስጦታ የተሰጠው ለእርሱ ብቻ ነው እንዴ?” “እኔ ከማን አንሼ ነው ሽማግሌነት ያልተመረጥኩት?” “በመንፈስ ቅዱስ እንጂ በቲዎሎጂ አይደለም” “እነርሱ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት አያምኑም”። ይህን ዓይነቱ ጤናማ ያልሆነ አስተያየትና ማጉረምረም በየቤተክርስትያኑ የምንሰማው ድምጽ ነው።

“በጌታ ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ እርሱም ከፍ ያደርጋችኋል” (ያዕቆብ 4፥10) የሚለውን ቃል ለመቀበል ብዙዎቻችንን ያስቸግረናል። ባለንበት ዘመንና ህብረተሰብ “ትሁት” መሆን “ደካማነት” መስሎ ስለሚታይ፥ እራሳችንን ዝቅ ማድረግ አንፈልግም። ታግሎ መጣል፣ ሮጦ መቅደም፣ ከሌላው ሁሉ ልቆና ጎልቶ መታየት የሰው ሁሉ ምርጫ ነው “የእኔ ዕውቀት፣ የእኔ ሃሳብ ይበልጣል፤ የእኔ ሚዛን ይሻላል፤ እኔን ምረጡኝ” ማለት እራስን ማተለቅ ሆኖ አይታይም። ይህን ዓይነቱ “የውድድርና የእሽቅድምድም” መንፈስ በዓለም ውስጥ አይሎ ቢታይ ይህን ያህል አይገርመንም። የሚያሳዝነው ግን በአማኞች መካከልም መታየቱ ነው። “ራስን ዝቅ ማደር” የሚከብደውና አስቸጋሪ የሚሆነው ለእኛ በዘመኑ ላለነው ክርስትያኖች ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ትምህርት ቤት ለሦስት ዓመት ተኩል የተማሩ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም እንኳን በጣም የከበደባቸውና መማር ያቃታቸው ትምህርት ስለ ነበረ በተለያየ ጊዜ “ከእኛ መካከል የሚበልጥ ማን ነው?” በማለት እርስ በርሳቸው ይጋጩ ነበር።

***“በጸጋ ስጦታ” መብለጣችንን የምናሳይበት አይደለም***

ዮሐንስ ያዕቆብና ጴጥሮስ በመገለጥ ተራራ ላይ የእግዚአብሔር ክብር ስላዩ ብቻ ከሌሎቹ ደቀ መዝሙርት እንበልጣለን በማለት እርስ በርሳቸው ይጨቃጨቁ ነበር። ኢየሱስም “በመንገድ ሳላችሁ የተከራከራችሁበት ነገር ምን ነበር?” ሲል ጠየቃቸው። ለጥያቄው መልስ ባይሰጡም ክርክራቸው “ከሁላችን የሚበልጥ ማን ነው?” የሚል ነበር። ኢየሱስም ይህንን አውቆ አንድ ሕጻን ልጅ በመካከላቸው አቁሞ “እንደዚህ ካሉት ሕጻናት አንዱን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል ሁሉ እኔን ብቻ ሳይሆን የላከኝንም ይቀበላል” (ማር 9፥37) አላቸው።
እግዚአብሔር በእኛም ዘመን ቤተክርስትያኑን ለማነጽ የጸጋ ስጦታውን ለልጆቹ ይሰጣል። የሚያሳዝነው ግን አንዳንዶቻችን የጸጋ ስጦታውን ለግል ጥቅማችን ስናውለው መታየታችን ነው። አንድ ጊዜ አንድ ክርስትያን ወንድም እንዲህ ሲል ጸለየ “ጌታ ሆይ! የፈውስ ስጦታ ስጠኝና፥ ከዚህ በፊት ያስቀየመኝ ወንድሜ ልጁ ታማበት እንድጸልይለት ወደ እኔ ይዟት እንዲመጣ አድርገው። እኔም ወንድሜን “እንደ አንተ ክፉነት ቢሆን ኖሮ ለልጅህ አልጸልይላትም ነበር፤ ግን ግድ የለም፤ እኔ እንደ አንተ አይደለሁም፤ ብዬ እጄን ጭኜ ስጸልይላት ልጁ ወዲያውኑ ትፈወስ፣ ይህን ሲያይም ይደነቅ” በማለት የሚመኘውን ምኞት በጸሎት መልክ አቀረበ። ነገሩ የሚያስቅና ሞኝነት የተቀላቀለበት ይምሰል እንጂ፥ ሁኔታው እውነት ነው። ከላይ የገለጽነውን ዓይነት አይምሰል እንጂ፥ እግዚአብሔር ቤተ ክርስትያኑን ለማነጽ ሲል በሚሰጠው የጸጋ ስጦታ አንዳንድ አማኞች ሊከብሩበትና ለግል ጥቅማቸው ሊያውሉት ሲሞክሩ ይታያሉ። “እኔ ስጸልይላት ተፈወሰች፤ እኔ እጄን ስጭንበት በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ፤ እኔ ስጸልይለት አጋንንቱ ጮሆ ወጣ” ብለን ብዙዎቻችን እናወራለን። የብዙዎቻችን ጉጉት በሽተኛው ከበሽታው መፈወሱና እግዚአብሔር መክበሩ ሳይሆን፥ የእኛ ስም መጠራቱ ነው። በአፋችን “እኔ ምንም አይደለሁም፤ ጌታ የሚቀመጥብኝ አህያ ብቻ ነኝ” እንበል እንጂ፥ ውስጣችን ሙገሳና አድናቆትን ይናፍቃል።

በዚህ ምክንያት ብዙዎቻችን ያልሆነውን “ሆነ” ያልተደረገውን “ተደረገ” ያልሰማነውን “እግዚአብሔር ተናገረኝ” ያላየነውን “እግዚአብሔር አሳየኝ” የምንለው። እግዚአብሔር አይናገረም፤ አያሳይም ማለታችን አይደለም። ለማለት የምንፈልገው በሰዎች ዓይን ተልቀን ለመታየት ስንል ብቻ ያልሆንነውን አንሁን ማለታችን ነው። የምናደርገው ለእግዚአብሔር ክብር ከሆነ፥ እግዚአብሔር የእኛ ድጋፍ ሳያስፈልገው፥ እራሱን ያከብራል።

እውነት ባልሆነና በተጋነነ ነገር እግዚአብሔር መክበር አይፈልግም።

"የአገልግሎት ዕድል አልተሰጠኝም" ብለን ቅሬታ ለምናሰማ፥ ጌታ እንድናገለግለው ከጠራንና በሩን ከከፈተልን፥ በምንም ዓይነት ሰው በሩን ሊዘጋብን እንደማይችል እንወቅ። የአገልግሎት በራችንን የሚከፍትና የሚዘጋ ሰው ካልሆነ በሌሎች ላይ የማጉረምረምና የቅሬታ ድምጽ ማሰማቱ የክርትና ሕይወታችንን ይጎዳል። ሰው አገልግሎት ሰጪና ከልካይ ስላልሆነ፥ ደጅ መጥናትና እጅ መንሳት አያስፈልገንም። አገልግሎት ለጌታ ክብር እንጂ ለራስ ጥቅም አለመሆኑን ካመንን፥ የአገልግሎት በር አልተከፈተልንም ብለን አናዝንም፤ ወይንም የተዘጋውን በር በኃይላችን ለመክፈት አንሞክርም። በየአብያተ ክርስቲያናቱ፥ በምዕመናኑ መካከል ባለው ውድድር ምክንያት አንዱ ሲወጣ፥ ሌላው ሲወርድ፣ አንዱ ሲሾም፥ ሌላው ሲሻር ይታያል። በሥልጣን ላይ ያለውም፥ የያዘውን ቦታ ላለመልቀቅ የሚያደርገው ትንንቅ ቀላል አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል ግን "በጌታ ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፥ እርሱም ከፍ ያደርጋችኋል" ሲል ይመክረናል (ያዕቆብ 4፥10)።

## የጸጋ ስጦታ የተሰጠን እንድንታበይበት አይደለም

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣቸውን የጸጋ ስጦታ በአግባቡ በመጠቀም ፈንታ እርስ በርሳቸው መፎካከሪያና መወዳደሪያ ያደርጉት ነበር። "እኛ ከእነ እከሌ የበለጠ በቋንቋ እንናገራለን" በማለት እራሳቸውን ከሌሎች አተልቀው ያዩ ነበር። ጳውሎስንም እንኳን "በቋንቋ የእኛን ያህል አይናገርም" ብለው ያሙት ነበር። ለዚህ ነው ጵውሎስ "እኔ ከሁላችሁ ይበልጥ በአዲስ ቋንቋ ስለምናገር እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ" (1 ቆሮ 14፥18) ያላቸው። ይህ ችግር የቆሮንቶስ ቤተ ክርትያን ብቻ ሳይሆን የእኛም ችግር ነው። እኔና ጓደኞቼ በዕድሜም ሆነ በክርስትና ሕይወታችን ልጆች በነበርንበት ዘመን፥ "በመንፈስ ቅዱስ" ተሞልተናል፤ እኛ ከእናንተ ይበልጣ እናውቃለን፤ እኛ ማስተማረን አለብን፤ እኛ መሪዎች መሆን አለብን" በማለት መንፈሳዊ መሪዎቻችንን እረፍት ነሳናቸው። በመጨረሻም ቤተ ክርስትያኑን ጥለንላቸው ወጣን። ታዲያ ይሄ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው? በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው የሚያሳየው የክርስትና ባህሪ ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወታችን አለመብሰላችንን የሚያሳይ ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የኛን ዓይነት አስተያየት የሌላቸውን ምንም ያህል የክርስትና ሕይወታቸው እንደ ጸሀይ ደምቆ ቢያበራም፥ "መነፈስ ቅዱስ የለባቸው፤ ደረቆች ናቸው" በማለት እንንቃቸው ነበር። ሌላውን ዝቅ አድርጎ ማየት፥ "እኔ ከሌላው የተሻልኩ ነኝ" ማለት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው የሚያሳየው ባህሪ ሳይሆን ትዕቢት ነው። "እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይንቃል፤ ለትሁታን ግን ሞገስን ይሰጣል" (ምሳሌ 3፥34) ይላል።

## አገልግሎት መክበርያ አይደለም

ያዕቆብና ዮሐንስ አንድ ጊዜ ወደ ኢየሱስ ቀርበው "በመንግሥትህ ክብር አንዳችን በቀኝህ አንዳንችን በግራህ እንድንቀመጥ ፍቀድልን" አሉት (ማር 10፥37)። የቀሩት ደቀ መዛምሩት ይህንን ሰምተው በያዕቆብና በዮሐንስ ላይ ተቆጡ። ኢየሱስም ይህን ተርድቶ "ከመካከላችሁ ትልቅ ሊሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ መሆን አለበት፤ እንዲሁም ከመካከላችሁ የበላይ ሊሆን የሚፈልግ የሁሉም አገልጋይ ይሁን" አላቸው (የማር. 10፥43-45)። እኛም በማናገለግለው ሕዝብ ፊት እግዚአብሔር ሞገስንና ጸጋን ሲያበዛልን አገልጋዮቻቸው በመሆን ፈንታ ገዢዎቻቸው ለመሆን እንድንሞክር እንጠንቀቅ። መንፈስ ቅዱስ የሰጠንን የጸጋ ስጦታ ለራስ ጥቅም፥ ለራስ ክብር ማዋል አደጋኛ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የመንፈስ ቅዱስ ስጣትን ከሐዋርያት እጅ በገንዘብ ለመግዛት የሞከረው ሲሞን ነው። "ሐዋርያት እጆቻቸውን ሲጭኑባቸው መንፈስ ቅዱስ ለሰዎቹ መሰጠቱን ሲሞን ባየ ጊዜ ገንዘብ አመጣለቸውና፥ እኔም እጄን የምጭንበት ሰው መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ" (የሐዋ ሥራ 8፥18)። ሲሞን ስጦታውን የተመኘው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊያገለግልበት ሳይሆን ለግል ጥቅሙ ነበር። ይሄ የሲሞን ችግር ብቻ ሳይሆን የብዙዎቻችን ችግር ነው።

## ከፍ ለማለት ዝቅ እንበል

ደቀ መዛሙርት የመጨረሻውን እራት ከክርስቶስ ጋር ለመብላት በተሰበሰቡበት ጊዜ "ከሁላችን የሚበልጥ ማን ነው? እያሉ እርስ በርሳቸው ይከራከሩ ነበር" (የሉቃስ 22፥24)። ኢየሱስም "ይልቅስ ከእናንተ መካከል ትልቅ የሆነ እንደ ትንሽ ይሁን፤ አለቃ የሆነም እንደ አገልጋይ ይሁን" (ሉቃ 22፥26) ሲል መለሰላቸው። ያ ገለጻ ብቻ እንደማይለውጣቸው የተረዳው ኢየሱስ ጎንበስ ብሎ እግሮቻቸውን በማጠብ ትህትናን በሥራ ላይ አውሎ አሳያቸው። ኤፍ ቢ ማየር "ምድራዊ ዙፋን የተሠሩት ወደ ላይ በሚያወጡት ደርጃዎች ሲሆን፥ የዘለዓለማዊ መንግሥት ዙፋን ግን የተሠሩት ወደ ታች በሚያወርዱ ደርጃዎች ነው። ከፍ ለማለት ወደ ታች ዝቅ፥ ቀጥ ብሎ ለመቆም መጎንበስ የጌታችን የዙፋን ተካፋይ ለመሆን እንደ ተራ አገልጋይ ወገባችንን ታጥቀን የደቀ መዛሙርቱን እግሮች ማጠብ ይገባናል" አለ። ራስን ዝቅ ማድረግ ትንሽነት ወይንም ደካማነት አይደለም። የራስን ደካማነት መገንዘብ፥ የአሸናፊ ሕይወት መግቢያ ነው። ከራስ ትምክህት ነጻ ስንሆን፥ ያኔ ጌታ ለክብሩ ይጠቀምብናል።

የእግዚአብሔር ሕግ እንደ ሰው ሕግ፥ የእግዚአብሔር አሠራር እንደ ሰው አሠራር አይደለም። የዓለም ሕግ “እራስህን ለማሳደግ ከፈለግህ፥ በልጠህ፣ ተሽለህ ለመታየት ሞክር” ይላል። የእግዚአብሔር ሕግ ግን “ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል” (ሉቃስ 18፥14) ይላል። ይህንን ኢየሱስ በንግግር ብቻ ሳይሆን በሕይወቱ ኖሮ አሳይቶናል። “እንደ ሰው ሆኖም በትህትና ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት ድረስ፥ ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ” ይላል (ፊሊ. 2፥8)።

**በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ትሁት ነው**

ፍላቨል የተባለው ጸሐፊ “እግዚአብሔርን በቅጡ የሚያውቅ ሰው “ትሁት” ይሆናል፤ እንዲሁም ማንነቱን በደንብ የተረዳ ሰው “እራሱን ማተለቅ” አይችልም” አለ። የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ ክብርና ገናናነት በቅጡ የገባው ሰው እራሱን ከእግሩ ሥር ዝቅ ያደርጋል። “እንግዲህ እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ፥ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ ሥር ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ” ይላል (1ኛ ጴጥ 5፥6)። በመጽሀፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን የክብሩን መገለጥ በግልጽ ይዩ ሁሉ እራሳቸውን እንደናቁና እራሳቸውን ዝቅ እንዳደረጉ እናያለን።

..............................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**